**የአገር መከላከያ ጃኗሪ 11 ቀን በኖርዌይ የማንቂያ ደውሎችን ይሞክራል**

የአገር መከላከያ በዓመት ሁለት ጊዜ፣ ጃኗሪና ጁን ላይ የማንቂያ ደውሎችን (የአውሮፕላን ደውሎችን) መስራታቸውን ሞክሮ የተበላሹትን ይጠግናል። ጃኗሪ 11 ቀን እኩለ ቀን (12 ሰዓት) ላይ የማንቂያ ደውሎችን ይሞክራል (አስፈላጊ መልዕክት / መረጃ ይፈልጉ) ሲሆን፣ ይህም የማስጠንቀቂያ ደውሎች በሚገኙባቸው ወረዳዎች ሁሉ ይደረጋል።

**የማስጠንቀቂያ ደወሉ**

የሚደወለውም በሶስት ተከፍሎ በየአንድ ደቂቃ ቆይታ ነው። ደውሉ ማለት መረጃ ፈልግ ማለት ሲሆን ይህም ለምሳሌ፣ ከሬድዮ፣ ቲቪ፣ ጋዜጣ፣ ከመንግስታዊ ድህረ ገጾችና ከማህበራዊ ድህረ ገጾች ነው።

**የማንቂያ ደውሎች**

ኖርዌይ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች 1 250 የሚሆኑ የማንቂያ ደውሎች አሉ፣ እነዚህም በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ህዝቡን ያስጠነቅቃሉ። የማስጠንቀቂያ ደውሎቹ በአብዛኛው በከተማና ህዝብ በብዛት በሚኖርባቸው ቦታዎች የሚገኙ ሲሆን በግምት ግማሹ ህዝብ ይሰማቸዋል። የማንቂያ ደውሎቹ በጦርነትና በሰላም ጊዜም አገልግሎት ላይ ይውላሉ።